

ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም

**በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡**

ለእስራኤል መንግስት
<u>ቴላቪቭ</u>

**<u>ጥብቅ ማሳሰቢያ (በድጋሜ የተላከ)</u>**

አንተ የተከበርክ የእሥራእል መንግስት ሆይ! ከያዕቆብ፣ ከዳዊት እና ከታቦተ ጽዮን አምላክ የተላከ መልዕክትና አደራ ተቀበል፡፡ ኢትዮጵያን እዳትረሳ አስታውስ አደራ ተጥሎብሃል፡፡ የቅዱስ ዳዊት የሰሎሞን አምላክ የቀዳማዊ ምኒልክ አምላክ የጠበቀ አደራ ጥሉብሃል፡፡ ኤርትራንና ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ሽምግልና ተሰጥቶሃል፡፡ ኤርትራ ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ ኤርትራ ተብላ መጠራቷንና ኤርትራ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር መሆኗን አውጅላት፡፡

የኤርትራ መንግሥት ጉዳይ አብቅቶለታል፡፡ ባለፉት ዓመታት የሸማግሌው የኤሊን ልጆች ምግባርና አርአያ በእናት ሀገር በኢትዮጵያ ላይ ተግብሯል። ፈጽሟል። ትምክህቱና ኃይሉ ተሟጥጧል። የኢትዮጵያ መንግስት ከእስራኤል መንግስት ጋር ይነጋገር። የኤርትራ መንግስት ልቡ ፈርሷል። ሐሞቱ ፈስሷል። ግራ ተጋብቷል። ኢሳይያስ አፈወርቂ ተቀስፏል። ኃይል የሥላሴ ነው። እንደ አፍኒንና ፊንሐስ እጁን ለእግዚአብሔር ሰጥቷል።

በኢትዮጵያ በኩል የአፄ ፋሲል፣ የአፄ ቴዎድሮስ፣ የአፄ ዮሐንስ፣ የዳግማዊ ምኒልክ፣ የአፄ ዘርዐያዕቆብና የታቦተ ጽዮን አምላክ ኢትዮጵያን እዳትረሳት ብሎኻል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ አድርጎ ቅዱስ ሚካኤል ሹሞልኻል፡፡ አንተ የእሥራኤል መንግስት ሆይ! ይህ ታላቅ አደራ ተጥሎብኻል፡፡ በፍጥነት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የቀረቤታ ንግግር አድርግ፡፡ ጊዜ የለም ብለናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ለአንተም ታጋይ ተቃራኒ ይነሳብኻል፡፡ እንዳይብስብህ ቅንነትና በጎነት ይሻልኻል፡፡ ሁሉን እንዳልሰማህ እንዳላወቅህ አትሁን፡፡ ጀሮ ዳባ ልበስ ብለህ እዳትዘናጋ እያልን በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

**ፈቃደ እግዚአብሔር ከኢትዮጵያና ከእስራኤል ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን፡፡**

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

  <u>ኢትዮጵያ፤አዲስ አበባ</u>

- <u>ለኤርትራ ሕዝብ፤አስመራ</u>